# የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ብሔራዊ ፖሊሲ

*ሚያዝያ 16 ቀን 1990 ዓ.ም.*

ብራና ማተሚያ ድርጅት

*የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ብሔራዊ ፖሊሲ*

## 1. *መቅድም*

**1.1** *ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የበርካታ የግብርና ተክሎች መፍለቂያና መራቢያ ከሆኑት ዋና የጀነቲክ ሀብት ማዕከሎች አንዷ ከመሆንዋም በተጨማሪ ሰፊ የዱር በቀል ዕፀዋት፣ የእንስሳትና የጥቃቅን ሕዋሳት ጀነቲክ ሀብት ባለቤት ነች። ይህ የጀነቲክ ሀብት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ እድገት ወሳኝ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ነገር ግን ይህ ሀብት በአሁኑ ጊዜ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት በመመናመንና ተፈጥሮአዊ ይዘቱም በመዳከም ላይ በመሆኑ መተኪያ በማይገኝለት ሁኔታ ለጥፋት በመደረግ ላይ ነው። ይህን የሕይወታዊ ሀብት ጥፋት መንግሥት በደንብ ተገንዝቦታል። እያሰበውም መጥቷል። ስለዚህ ይህ የጀነቲክ ሀብታችንን ለመጠበቅ ቀጣይነት ባለው መልክ ለማዳበርና ለመጠቀም የሚያስችል አስቸኳይ ብሔራዊ እርምጃ መውሰድንና ተገቢውን ሥርዓት መዘርጋትን ይጠይቃል።*

**1.2** *የዕፀዋት፣ የእንስሳትና የጥቃቅን ሕዋሳት የጀነቲክ ሀብት ወደ ሀገር ማስገባትን፤ ከሀገር ማስወጣትንና የልውውጥ ተግባራትን በተመለከተ አጠቃላይ የፖሊሲ መመሪያ እና ተገቢው ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት የተለያዩ ዝርያዎች ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባቱና ከሀገር የማስወጣቱ እንቅስቃሴ ቁጥጥር የጐደለውና ያልተቀናጀ መሆን፣ይህ ሁኔታ ደግሞ ውድ ከሆኑ ሀገር በቀል የጀነቲክ ሀብቶች የሚገኙትን ጥቅሞች ሊያስቀር ከመቻሉም በተጨማሪ ምንነታቸው ያልተረጋገጠ ዝርያዎች ከዚህ ጋር በተያያዘም የዝርያ በሽታዎች፣ ተባዮችና አረሞች ወደ ሀገር ውስጥ መግባትን አስከትሏል፤ እያስከተለም ነው።*

**1.3** *የጀነቲክ ሀብትን በአስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅን፣ ሚዛናዊ በሆነ ስልት ማዳበርንና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መጠቀምን በተመለከተ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገባቸው ብሔራዊ እርምጃዎች አንዱ ብሔራዊ አቋምን በተገቢው የመንግሥት ፖሊሲ መግለጽ ነው። ይህንንም እውን ለማድረግና የሕይወታዊ ሀብትን መጠበቅ ለአጠቃላይ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እድገትና ለዘላቂ የአካባቢ ጥበቃ ዓላማዎች መሳካት አስፈላጊ ከሆኑ ቀዳሚ ሁኔታዎች አንዱ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የሕይወታዊ ሀብት ብሔራዊ ፖሊሲ ወጥቷል። ስለዚህ የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃ፣ ተገቢ አያያዝና አጠቃቀም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ በፖሊሲ በሕግና በብሔራዊ አቅም ግንባታ ሊደገፍና ሊጠናከር ይገባል።*

## 2. *ዓላማዎች*

**2.1** *የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ብሔራዊ ፖሊሲ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።*

- *የኢትዮጵያ የዕፀዋት፣ የእንስሳትና የጥቃቅን ሕዋሳት ጀነቲክ ሀብቶችና አጠቃላይ ሥርዓተ ምህዳሮች መጠበቃቸውን፣ መልማታቸውን፣ በአግባቡ መያዛቸውንና በዘላቂነት በጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ*

- *በጀነቲክ ሀብት ላይ የብሔራዊ ባለቤትነት መከበርን፣ ይህን ሀብት በሚዛናዊነት መለዋወጥን፣ ጉዳት በማያስከትል መልኩ ማንቀሳቀስንና በአጠቃላይ ተገቢ አያያዙን የሚያረጋግጥ ዘዴ መቀየስ*

* በሀገሪቱ ሕጐችና ደንቦች እንዲሁም ሀገሪቱ ባደረገቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የሀገሪቱ የጀነቲክ ሀብቶች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ በማሰባሰብና በማስተዋወቅ እንዲሁም ከሀገር የወጣውን በማስመለስ ማበልፀግ ማበረታታት:: በተጨማሪም ባሕላዊ እውቀትና የጀነቲክ ሀብት በጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ከሚገኘው ጥቅም ተካፋይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

* በሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና መዳበር ሂደት አግባብ ባላቸው ድርጅቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ትስስርና ቅንጅት ለማረጋገጥ የሚያስችል ተግባራዊና ቀልጣፋ መዋቅር መፍጠር፤

* የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ልማት መዳበርንና ዘለቄታ ያለው አጠቃቀምን ውጤታማ ለማድረግ አካባቢያዊና ዓለምአቀፋዊ ትብብርን ማበረታታት::

## 3. የፖሊሲ መመሪያዎች

የተጠቀሱትን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት የፖሊሲ መመሪያዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

3.1 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት የሀገሪቱን የሕይወታዊ ሀብት ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና ዘላቂነት ባለው የአጠቃቀም ሥርዓት መሠረት ለማራመድ የሚያስችል አዲስ ሕግና ደንብ እንደ አስፈላጊነቱ ያወጣል እስከአሁን የሚሠራባቸውን ሕጐችና ደንቦች ያሻሽላል::

3.2 መንግሥት ለዕፀዋት ለእንስሳትና ለጥቃቅን ሕዋሳት ጀነቲክ ሀብት ቅኝት፣ አሰባሰብ፣ አጠባበቅ፣ የባህሪያት ትንተና፣ ግምገማና አጠቃቀም እንዲሁም ለጥናትና ምርምር መዳበር ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል::

3.3 ኢትዮጵያ በሕይወታዊ ሀብቷ ላይ የባለቤትነት መብት ያላት መሆኑን በመገንዘብ ይህን የጀነቲክ ሀብት አስመልክቶ የሚከናወን ማንኛውም የቅኝት፣ የምዝገባ፣ የአሰባሰብ፣ የማንቀሳቀስ፣ የመለዋወጥ፣ ወደ ሀገር የማስመለስ፣ እንዲሁም የመጠቀም ተግባር በሀገሪቱ ሕግና ደንብ እንዲሁም በሁለት ወገንና ወይም ከሁለት በላይ ከሆኑ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ስምምነቶች መሠረት ይሆናል::

3.4 ይህንን ፖሊሲ የሚያስፈጽም አካል ማቋቋም

3.5 የፌደራልና የክልላዊ መንግሥታት የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀም ነክ ትምህርቶች በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በሚገባ መዋሃዳቸውንና የሕይወታዊ ሀብት ጉዳዮችን በተመለከተ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በአጠቃላይ በሕብረተሰብ ዘንድ ተገቢው ግንዛቤ መስረፁን ማረጋገጥ::

3.6 ባህላዊ የሕይወታዊ ሀብት የጥበቃና የአጠቃቀም ስልቶች እንዲሁም አገር በቀል እውቀቶች በሚገባ ተሰብስበው፣ ተመዝግበው፣ ተጠንተውና ተሻሽለው በጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ::

3.7 በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሕብረተሰቡን ተሳትፎ እንዲሁም የአካባቢውን ሕዝብ የሀብት ባለቤትነት የሚያረጋግጡና ከእነዚህም በጋራና

በአስተማማኝ እንክብካቤ ከሚያዙ የተፈጥሮ ሀብቶች ለሕዝቡ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ለማስገኘት የሚያስችሉ በሕብረተሰቡ ላይ የተመሰረቱ ሥርዓቶች እንዲኖሩ ማድረግ::

**3.8** የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጠንቶ በሚቀርብለት የውሣኔ ሀሳብ መሠረት የዘቦታ ጥበቃዎችን (ብሔራዊ ፖርኮችንና ሌሎች የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃ ቦታዎችን) በየደረጃው በፌደራላዊ መንግሥት ወይም በክልላዊ መንግሥታት ሥር እንዲተዳደሩና እንዲመሩ ያደርጋል::

**3.9** የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ብሔራዊ ፖሊሲ ከብሔራዊ የኢኮኖሚ፣ የእርሻ፣ የኢንዱስትሪ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሥነ ሕዝብና፣ የከተማ፣ የሀይልና የህንጻ፣ የሀብት አያያዝና የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር የተዋሀደና በእነዚሁም የተደገፈ ይሆናል:: ዘላቂነት ያላቸው የማምረት ስርዓቶች መዳበርን ለማበረታታት፤ በእነዚህም ስርዓቶች አማካይነት በስነ ሕይወታዊ ሀብቶች ላይ የሚመጣውን ተጽእኖ ለመቀነስና የሚያስከትለውን ጉዳት ለማስወገድ የእነዚህ ዘርፎች ፖሊሲዎች እርስ በርሳቸው የተገናዘቡና የተጣጣሙ እንዲሆኑ ያደርጋል::

**3.10** በሀገሪቱ ውስጥ ከሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ጋር የተያያዙ የተለያዩ ተግባራትን ለማቀድ፣ ለማዳበርና ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ እንዲሁም የተቀናጀ ብሔራዊ የሕይወታዊ ሀብት መርሃ ግብር ለመፍጠር ለተግባራዊነት አመቺ የሆነ የመገናኛ ሥርዓት ይዘረጋል::

**3.11** ጠንካራ የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃ፣ ምርምርና አጠቃቀም ለማከናወን በስፋት የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በጥናትና ምርምር፣ በመሠረተ ልማት ድጋፍና በአገልግሎት ሰጭ መሳሪያዎች ጠንካራ ብሔራዊ ብቃትና ችሎታ ወሳኞች ናቸው:: ስለዚህም መንግሥት ለሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር፣ ለብሔራዊ ብቃትና ችሎታ ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል:: የጀነቲክ ሀብት እንክብካቤና ዘላቂ አጠቃቀም የተለያዩ ሙያዎችን የሚያሳትፍና የበርካታ ሙያተኞችን የተቀናጀ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ መንግሥት ለሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና መዳበር አግባብ ያላቸው ሙያተኞችን የማሰልጠንና የማደራጀቱን ጉዳይ በቅርብ ይከታተላል::

**3.12** በሀገሪቷ የሕይወታዊ ሀብት አጠባበቅን ዘላቂ አጠቃቀምን በተመለከተ መረጃ የማሰባሰብ፣ የመመዝገብ፣ የማደራጀትና ለተጠቃሚዎች የማሰራጨት ችሎታና ብቃት ያለው ብሔራዊ የሕይወታዊ ሀብት መረጃና ሰነድ ማደራጃ ሥርዓት ይዘረጋል::

**3.13** የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃ ልማትና አጠቃቀምን በተመለከተ መንግሥት ያፀደቃቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማስፈፀም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

**3.14** ፌደራላዊ መንግሥትና የክልል መንግሥታት ከሕይወታዊ ሀብት የሚሰበስቡት ገቢ ለሕይወታዊ ሀብት አጠባበቅ፣ ልማትና አስተዳደር እንዲሁም በአጠባበቁና በእንክብካቤው ላይ ተሳትፎ ለሚያደርጉ የአካባቢ ሕብረተሰብ ጥቅም እንዲውል ያደርጋል::

# National Policy on Biodiversity Conservation and Research

**National Policy on Biodiversity Conservation and Research**

## 1. Preamble

1.1 Ethiopia, being one of the major centres of origin/diversity for many cultivated plant species, has also immense wealth of wild plant, animal and microbial genetic resources. These genetic resources are vital to the economic, social and environmental development of the country. However, this endowment of genetic resources is threatened by irretrievable loss of biodiversity as a result of , inter alia, resource mismanagement and degradation leading to genetic erosion. The government has duly recognized and is concerned about this phenomenon. The situation, therefore, requires an urgent national action to ensure the conservation of genetic resources and develop rational systems for their development and sustainable use.

1.2 Lack of comprehensive policy guidelines, awareness and appreciation on plant, animal and microbial genetic resources importation, exportation and exchange activities has resulted in the movement of genetic resources into and out of the country in an unregulated and uncoordinated manner. This has resulted in the loss of benefits from valuable indigenous genetic resources and in the introduction of unverified genetic materials, diseases, pests and weeds in to the country.

1.3 One of the priority areas of national action towards the effective conservation, rational development and sustainable utilization of genetic resources is a national commitment through an appropriate government policy. To this end, the national policy on Biodiversity Conservation and Development is formulated based on the rationale that the conservation of biodiversity is one of the conditions of the overall socio economic development and sustainable environmental management goals. Hence, because of its vital importance in the socio economic well being of the Ethiopia people, the conservation, proper management and the use of biodiversity need to be supported by policy, legislation and national capacity building.

## 2. Objecitives

2.1 The objectives of the National Policy for Biodiversity Conservation and Research are to:

- ensure that the Ethiopian plant, animal and microbial genetic resources and essential ecosystems as a whole are conserved, developed, managed and sustainably utilized;

- assert national sovereignty over genetic resources and develop a mechanism for a fair exchange, safe movement and proper management of these resources;

- enrich the genetic resources of the country through introduction (from abroad and within the country), repatriation and restoration in accordance with the laws and regulations of the country and according to bilateral and/or multilateral agreements the country has made;

- build national scientific capacities and capabilities to explore, collect, conserve, characterize, evaluate and utilize the biodiversity of the country;

- integrate biodiversity conservation and development programs into Federal and Regional agricultural, health, industrial and overall national economic development strategies and plans;

- recognize, foster and augment the indigenous knowledge and methods relevant to the conservation, development and sustainable use of biodiversity, and promote and encourage the development and putting into practice of new and emerging technologies such as biotechnology;

- encourage the participation and support of local communities in biodiversity conservation, development and utilization. Furthermore, ensure that they share the benefit accrued as a result of using indigenous knowledge and/or germplasm;

- create a functional and efficient organizational structure to ensure inter institutional linkage and coordination in biodiversity conservation, development and utilization;

- promote regional and international cooperation in biodiversity conservation, development and sustainable use;

## 3. Policy Directives

In order to realize the objectives started, the following policy directives will be followed:-

3.1 the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia will enact, and update as necessary, legislation to protect; conserve and sustainably utilize the biological resources in Ethiopia.

3.2 The government will give due attention to the exploration, collection, conservation, characterization, evaluation and utilization as well as to promoting research and development of the flora, fauna and microbial genetic resources.

3.3 recognizing the fact that Ethiopia has sovereign rights over its genetic resources any exploration, inventory, collection, movement exchange, repatriation and the use of these genetic resources will be governed by the laws and regulations of the country as well as bilateral and/or multilateral agreements.

3.4 Establish a body that enforces this policy,

3.5 The Federal and Regional Governments will ensure the integration of biodiversity conservation and sustainable use related education into the educational system and the creation of awareness on biodiversity issues at the individual, family and community levels.

3.6 Traditional conservation and utilization systems and indigenous knowledge on biodiversity will be surveyed, assessed, documented, studied, improved and utilized.

3.7 Community participatory approach in the decision making processes and the creation of community based systems which recognize resource rights of the local people and enable them to get economic benefits from jointly and sustaiably managed natural resources will be ensured.

3.8 the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia will put the administration and management of *in-situ* conservation areas (national parks and other categories of designated protected areas) under the Federal or Regional Governments.

3.9 The National Policy for Biodiversity Conservation and Research will be integrated with and supported by policies and strategies on the national economy, agriculture, industry health, education, population and urbanization, energy and construction, resource management and environmental protection. The policies in these sectors shall be harmonized to enhance sustainable production systems and to encourage the development of alternative resources and sustainable management systems in order to reduce the pressure on and avoid degradation of the biological resources.

3.10 In order to plan, develop and reorient the different biodiversity conservation and development related activities in the country and create an integrated national biodiversity program, a functional national biodiversity networking system will be created.

3.11 Strong national capacities and capabilities in scientific personnel, research infrastructure, funding and facilities are essential to undertake active biodiversity conservation, research and development. Hence, the Government will give high priorities for building national capacities and capabilities in biodiversity conservation and development. Since the management and sustainable use of

genetic resources is a multidisciplinary field requiring an integrated effort of a range of experts, the Government will follow up the training and organization of professionals in those areas/disciplines relevant to biodiversity conservation and development.

3.12 A national biodiversity information and documentation system that is capable of acquiring, documenting, processing and disseminating information relevant to the conservation and sustainable utilization of the country's biodiversity to potential users will be established.

3.13 The government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall take the necessary steps to discharge its obligations under international treaties concerning the protection, conservation or utilization of biological resources.

3.14 The federal and regional governments shall receive and distribute revenues generated from biodiversity exclusively for the benefit of communities associated with or participating in the conservation of biological resources, and the costs of administering, developing and managing biodiversity.